Coronavirus pandemic: Technical lessons learned from Germany

# በጀርመን የገባውን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን በተመለከተ ያለው ቴክኒካዊና ተቋማዊ ልምድና አስተያየት - ክፍል 5

## ለተከበራቹህ ወገኖች

የኮሮና ልምድ ከጀርመን 14.06.2020

**ይዘት**- [ኢኮኖሚዊ እይታ | ያልተጎዳ ዘርፍ ወይም በወረርሽኙ ያተረፉ | ኢኮኖሚውን ለማንቃቃት የተወሰዱ እርምጃዎች | ድጎማ እና ቅድመ ሁኔታዎች | ዴሞክራሲ እና የፖለቲካ አመራር | የስራ ባህል መቀየር | የጀርመን ጠረፍ | የገደቦች መላላት - የንፅህና ፕላን | ቴያትር እና ፊልም | መዝናጋት እና ሰላማዊ ሰልፎች | አሸብላይ መልዕክቶች እና የሴራ አይዲውሎጂ | የበጎ ፈቃድ አገልገሎት | ለይቶ ማቆያ፣ የኮሮና ቫይረስ ሪፖርት፣ የጤና ባለሙያዎች ]

*ከአለፈው በመቀጠል* ለኢትዮጵያ ቴክኒካዊ ይዘቱ እና ለአጠቃላይ ግንዛቤ በአጣቃሽነት እንዲረዳ በማሰብ ከተጓዳኝ ነጥቦች ጋር **ክፍል አምስትን** አቀርባለሁ።

በጀርመን የኮሮና ቫይረስ / ኮቪድ 19 ወረርሽኝ ሲቀንስ፣ በኢትዮጵያ ደግሞ ወደ ብዜታዊ እድገት (Exponential Growth) በመቀየር እየጨመረ መምጣቱ በጀርመን መጋቢት ላይ ብዜታዊ እድገት ሲጀምረው የነበርውን አይነት ሁኔታን እያስታወሰን ነው። ኢትዮጵያን ልዩ የሚያደርገው በቅርቡ የሚኞቹ ሁኔታ ሲታይ ታውቀው፣ እየታከሙ ህይወታቸው ያለፉት ሳይሆን ከሞቱ በኋላ የተገኘባቸው ቁጥሩ መጨመሩ ነው። ይህ ሁኔታ በአንፃሩ በጀርመን ከሞቱት ከ8ሺ በላይ ሰዎች ላይ በብዛት ሲሰማ አልታየም። ለዚህም ያለው የጤና ስረዓት፣ የአስተሳሰብ ባህል፣ የመርጃ ፍሰት እና የኢኮኖሚ የእድገት ደርጃ ወሳኝ ይመስለኛል። ለኢትዮጵያ ይህ ጉዳቱ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል።

### 1. ኢኮኖሚዊ እይታ - የአየር እና የመኪና እንዱስትሪ

ስመ ጥር የሆነውና ከአለም የአየር መንገዶች በቀዳሚነት የሚገኘው ሉፍታንዛ 9 ቢሊዮን ዩሮ ከመንግስት ቢደጎምም 22 ሺ የስራ መደብ ለመቀነስ ማሰቡ አሳሳቢ ሆኗል። በረራዎቹም እስከ 4% ወርደው ነበር። ሉፍታንዛ በአመት ብቻ ከ35 ቢልዩን ዩሮ በላይ ገቢ ያለው እና 361 አውሮፕላኖችን የያዘ ግዙፍ አየር መንገድ ነው። ለፈረንሣይ አየር መንገድ ኤርፍራንስም የፈረንሳይ መንግሥት ተመሳሳይ ድጋፍ አደርጓል ፡፡

የመኪና ኢንዱስትሪዎችም በተመሳሳይ በብዙ ሺ የሚቆጠር የስራ መደቦችን እንደሚቀነሱ ይጠበቃል። የጀርመን የመኪና ኢንዱስትሪ የጭነት እና ልዩ መኪናዎችን ሳይጨምር እስከ 5 ሚሊዮን የቤት መኪናዎችን ጀርመን ውስጥ ብቻ በዓመት ያመርታል (በሌላ አህጉራት ያሉትን ፕላንቶች ሳይጨምር)። በጀርመን ከሰባት ሰዎች አንዱ በመኪና እንዱስትሪ ወስጥ ይሰራል። ከመኪና ጋር በተያያዘ በቅርቡ ትልቁ የመኪና አከራይ ኩባንያ ሄርትዝ (Herz) በአሜሪካ የኮሮና ቀውስ ውስጥ የተነሳ ለኪሳራ (insolvency) ተዳርጓል፡፡

የአየር ካርጎ ስርጭት ብዙም ባይጎዳም የአለም <u>የባህር ካርጎ</u> ላይ ግን መቀንስ ታይቷል። በአጠቃላይ የባህር ላይ ካርጎ በ500 መቶ የኮንቴነር መርከቦች ቀንሷል።

### 2. ኢኮኖሚ እይታ - የመጋራት ኢኮኖሚ

የመጋራት ኢኮኖሚን (Sharing Economy) ከወሰድነው በከፍተኛ ሁኔታ ተጎድቷል። የመጋራት ኢኮኖሚ የሚባሉት እንደ ኡበር (UBER) ቋሚ ያልሆነ የታክሲ ስራን በግል መኪና መጠቀምን፣ ኤርቢንቢ (Airbnb) መኖሪያ ቤትን ለአጭር ጊዜ በፕላት ፎርም ተጠቅሞ እንደ ሆቴል ማከራየት፣ ዊወርክ (WeWork) ስራ ቦታን መካፈል/ማከራየት፣ ካርሺሪንግ - መኪና ማጋራት የመሳሰሉት ናቸው።

## 3. ያልተጎዳ ዘርፍ ወይም በወረርሽኙ ያተረፉ (ከጤና እንዱስትሪ እና ተጓዳኝ ዘርፍ ውጭ)

በተገላቢጦሹ ደግሞ የርቀት ኢኮኖሚ (Distance Economy) የመባል የስም አዝማሚያን እያያዘ የመጣው ብዙ ሰዎች ሥራቸውን፣ ትምህርታቸውን ወይም የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያን ወደራሳቸው አራት ግድግዳዎች እንዲያሸጋገሩ የሚያደገርው አሰራር ነው፡፡ ከመጋቢት ጀምሮ የኦንላይን የችርቻሮ ንግድ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በሚያዝያ ወር ብቻ 18 በመቶ ገደማ አድጓል። እንደ አማዞን (Amazon) ያሉ የእንዱስትሪውን ከፍተኛ ድርሻ ወስደዋል። እዚህ ላይ በቀዳሚነት ከሚመሩት አንዱ ዙም (Zoom) በሚያዝያ 2020 ወር ውስጥ እስከ 300 ሚሊዮን የሚሆኑ የቪዲዮ ኮንፈረንሶችን ማካሄድ አስችሎአል። በዲሴምበር 2019 ይህ ቁጥር አስር ሚሊዮን ብቻ ነበር፡፡ የሃይል፣ የመብራት፣ የመሰረትዊ ፍጆታዎች፣ የምግብ አቅርቦት አልተጎዱም። ርካሽ የሆን የነዳጅ አቅርቦት እና የከባቢ አየር ብክለት ግዚያዊ ቅነሳ ሲታይ፣ የመብራት ሃይል በቤት ተጠቃሚነት በከፍተኛ ሁኔት ጨምሯል።

ግድበቱ ብዙውን ሰው በብስክሌት እንዲጠቀም ለማነቃቃት ችሏል። በዚህም የብስክሌት ተጠቃሚነት እና ግዢ ጨምሯል። በጀርመን ውስጥ ወደ 74 ሚሊዮን የሚቆጠሩ ብስክሌቶች አሉ ፡፡

የሴራ ቲዮሪ/አይዲውሎጂ እና የሳይበር ወንጀልም ጨምሯል። ለምሳሌ የመንግስትን ለአስቸኳይ እርዳታ የተዘጋጀ ድህረ ገፅን በማስመሰል በተዘጋጀ አጥማጅ ድህረ ገፅ (Phishing Page) በመጠቀም እዚያ ላይ ለአስቸኳይ እርዳታ ለማምልከት ሙሉ የግል እና የቢዝነስ ዳታዎቻቸወን በፎርም ላይ የሰጡትን ሰዎችን አጥምዶ በማሰብሰብ እና ይህንንም በዋናው የመንግስት የእርዳታ ገፅ ላይ እንደራስ አድርጎ በማቅረብ በሚሊየን የሚቆጠር ዩሮ ተዘርፏል።

## 4. ኢኮኖሚውን ለማንቃቃት የተወሰዱ እርምጃዎች

በቅርቡ የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ድርጅት (OECD) የዓለም ኢኮኖሚ እስከ 7.6 በመቶ እንደሚወርድ ይጠበቃል። በተከሰተው ወረርሽኝ ሳቢያ ዜጎች፣ ንግዶች እና አገሮች ከባድ እና የረጅም ጊዜ ችግሮችን መጋፈጥ ሊኖርባቸው እንደሚችል ይታወቃል። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ በኮሮና ወረርሽኝ የተከሰተው ቀውስ ለጤና እና ኢኮኖሚያዊ ሴክተሩ ታይቶ እንድማይታወቅ ተመዝግቧል፡፡

የጀርመን ኢኮኖሚ በዚህ አመት በ9.4% እንደሚቀንስ ሲታውቅ እስካሁን ድረስ በመቶ ቢሊዮኖች ቢደጎምም ይህ ድጎማ የኢኮኖሚውን ወደታች መውረድ በ 1.3 % ብቻ በማሻሻል ቅነሳው 8.1 % እንድሚያደርስው ነው የተተነበየው።

በአለፍው ተከታታይ ፅሁፎቼ ከጠቀስኩት በተጨማሪ መራሂ መንግስት ቻንስለር ሜርከል የዋጋ ታክስ (VAT) ከሐምሌ ወር ጀምሮ ለግማሽ ዓመት ከ 19 ወደ 16 በመቶ እንደሚቀንስ አስታውቀዋል። ይህም ኢኮኖሚውን እንደገና ከፍ ለማድረግ እና ግብይትን ለመጨመር የታሰበ ነው። ይህ የታክስ መቀንስ እርምጃ በኮሮና ቀውስ ውስጥ የሚገኘውን ኢኮኖሚ ለማነቃቃት ታስቦ  የጀርመን መንግስት ከዚህ በፊት ከተደረገው በተጨማሪ ከቀናት በፊት በሰኔ የፀደቀው የ130 ቢሊዮን ዩሮ የማነቃቂያ ድጎማ ጥቅል አካል ነው። የፋይናንስ ሚንስትሩ እንደተናገሩትም ይህ ድጎማ የአውሮፓን ኢኮኖሚን ጭምር ለማሳደግ ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል። የጀርመን ኢኮኖሚ ብቻውን መቆም አይችልም። ኢኮኖሚው ጠንክሮ እንዲቆይ 40% ምርቱን ኤክስፖርት መደረግ ይኖርበታል።

ይህንን በድጎማ የሚፈስውን የዕዳ ቁልል ለመመለስ ከአስር አመት በላይ ሊወስድ እንደሚችልም ይታመናል።

## 5. ድጎማ እና ቅድመ ሁኔታዎች

በሚያዝያ መጨረሻ 11ኛው ፕተርስበርግ የአየር ንብረት ውይይት ላይ ቻንስለር መርክል ለአየር ንብረት ተስማሚ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ማነቃቃትን ደግፈዋል። የፌደራል የአካባቢ አየር ኤጀንሲ በተጨማሪም በኮሮና ቀውስ ውስጥ ያሉት በርካታ የእርዳታ እቅዶች ከአየር ንብረት ጥበቃ ሁኔታዎች ጋር የተገናኙ እንዲሆኑ እና የአካባቢ ጥበቃ መዘንጋት እንደሌለበት ጥሪ አቅርቧል፡፡



Dr. Tsegaye Degineh, H: www.degineh.de, E:mail@degineh.de፣ T: @TsegayeD4, F: fam.degineh

መንግስት የሚሰጣቸውን ድጎማዎችንም ከቅድመ ሁኔታዎች ጋር በማያያዝ ማህበራዊ ግዴታዎችን፣ በተለይም ለአከባቢ አየር ጥበቃ አስትዋፅዎ እንዲያደርጉ በሚያስችል መልኩ እንዲቀርፁ እየታሰበበት ነው።

ኤርፍራንስን አየር መንገዱ "በዓለም ላይ በጣም ለአካባቢ አየር ተስማሚ አየር መንገድ መሆን አለበት" በማለት እስከ አራት ቢሊዮን ዩሮ የእርዳታ ፓኬጅ የፈረንሣይ መንግስት የከባቢ አየርን ከመጠበቅ ቅድመ ሁኔታ ጋር በማያያዝ አቅርቦለታል፡፡ ጀርመንም ለሉፋታንዛ በተመሳሳይ የእርዳታ ዕቅዱ የአካባቢ ጥበቃን "ሥነ-ምህዳራዊ ሁኔታዎች" በያዘ ድጋፎች እንዲሻሻል የጥሪ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

## 6. ዴሞክራሲ እና የፖለቲካ አመራር

እንደ ፌዴራል ጀርመን አይነት ብዙ ጊዜያቸውን በዴሞክራሲ ያሳለፉ አገሮች ገደቦችን በከፍተኛ አብላጫ እና በሚያስገርም መልኩ በትእግስት የመቀበል ችሎታ እንዳላቸው አሳይተዋል፡፡ በወረርሽኙም የፖለቲካ አመራር ትርጉም፣ ዘላቂነት፣ ወሳኝነት፣ የህዝብ ደህንነትን እና ኢኮኖሚን የመጥበቅ ኃላፊነት፣ ግሎባላይዜሽን እና አካባቢያዊነት ልዩ ትኩረት አግኝተዋል።

- የማዕከላዊ እና የተቀናጅ የፖለቲካ አመራር መመለስ

ቀውሱ ወደ ቀድሞው ማዕከላዊ የአመራር እና የስቴት ፖሊሲዎች ተምልሶ በመምጣት፣ የመንግስት ሚናን በመጨመር የግል ሴክተሩ እንቅስቃሴ በተቃራኒው እንዲዳከም አድርጎታል። ሰው በመንግስት እና በፖለቲካ ላይ ለረጅም ጊዜ ያጣውን እምነት በአብዛኛው ሊመልስለት ችሏል ፡፡

- አውሮፓ- አዲሰ ዓለም አቀፋዊ የበላይነትን ለመያዝ ማምራት

መጀመርያ ላይ በቀውሱ አደጋ ላይ የወደቀውን የአውሮፓ ኢኮኖሚ  ተጋግዞ መፍትሄ ለማምጣት ቢከብዳቸውም በፍጥነት መፍትሄ ተገኝቷል፡፡ የአውሮፓ ህብረት በችግሩ አልፈረስም። ችግሩ አዳዲስ ጥንካሬዎች እንዲያንፀባርቁ አድርጓቸዋል፡፡ የአውሮፓ የፋይናንስ ማረጋጊያ ስረዓት (ESM) 240 ቢሊዮን ዩሮ ለተጎዱት አገሮች አቅርቧል። ከሌሎቹ ጋረ ሳይመካከሩ የትኛውም ሀገር ጠርፉን ሊከፈት እና እንቅስቃሴዎችን ሊጀመሩም አይችልም፡፡ የመከላከያ ክትባትን በተናጠል ሳይሆን በጋር ለማግኘት ወደ 2.4 ቢሊዮን ዩሮ መድበዋል። ከዚህ አካሄድም  የአፍሪካ አገሮችም የጀመሩትን ኢንሺያትቭ በመቀጥል በህብረቱ ስር ሃይላቸውን በማሰባሰብ በጋራ መድሃኒትም ሆነ ክትባት ላይ ቢሰሩ እንደሚያዋጣቸው ያሳያል። የአውሮፓውያኑ ተምሳሌትነት በጥንካሬ እና በትብብር የተሞላ መሆኑን አረጋግጧል።

- ህዝበኝነት (Populism) መዳከም

የኮሮና ቀውስ ከዚህ በፊት በከፍተኛ ሁኔት በየቦታው እያንሰራራ የነበርውን ህዝበኝነት፣ የአክራሪነት እና ስሜት ቀስቃሽነት ህልውናን አሳንሶታል። ቫይረሱ ለመከላከል ሰውነትን ብቻ ሳይሆን፣ የአዕምሯዊ እና የፖለቲካ ብርታትን በተጓዳኙ እንዲፈጠር አስችሎአል ፡፡

## 7. የስራ ባህል መቀየር

የቤት ቤሮን እና ዲጂታል መሰርተ ልማትን የመጠቀሙ ሂደት በአጭር ጊዜ ለውጥ አምጥቷል። የታውቀው ኢኮኖሚስት ጆን ኬይንስ (John Maynard Keynes) ባንድ ወቅት  "ችግሩ አዲሱ ሀሳቦች ማምጣቱ ላይ ሳይሆን አሮጌዎቹን መተው ላይ ነው" - ያለውን ስናስታውስ በወረርሽኝ ምን ያህል ሰው የድሮን አስራር ያለ ረዥም ጊዜ መቸገር እየተወው መቀየሩ ምን ያህል ስኬትማ መሆኑን ያሳያል።

ኒውዚላንድ በሳምንት 4 ቀን ስራን መደበኛ ለማድረግ ያሰብችውን ሞዴል ጀርመንን ጨምሮ በተለያዩ አገሮች ለመወያያነት የቀረብ ነው። ይህ ሁኔታ ቱሪዝምን፣ ግብይትን እና ለጤና ተስማሚ የተሳለጠ የስራ፣ የቤተሰብ እና የዕረፍት ጊዜን ሊፈጥር ይቻላል።


Dr. Tsegaye Degineh, H: www.degineh.de, E:mail@degineh.de፣ T: @TsegayeD4, F: fam.degineh

## 8. የጀርመን ጠርፍ

ጀርመን ጠርፉን ከ15 June ለህብረቱ አገራት ክፍት ያደርጋል። ለሌሎች አገሮች እስከ 31 August ዝግ ሆኖ ሲቆይ፣ እንደሁኔታው ታይቶ በተናጠል የጀርመንን ዜጋ ለሚፈቅዱ እና ስትራቴጂያዊ ጉድኝት ላላቸው አገራት ሊከፈትም ይችላል።

## 9. የገደቦች መላላት - የንፅህና ፕላን (Hygiene Concept)

ንኪኪ ያልሆኑ የስፖርትን፣ ሱቆችን፣ ማዕከላትን፣ የቁንጅና ሳሎን ወይም የጤን ሳሎንን መልሶ የሚከፍት ከሆነ ለጤና ቢሮ በመጀመሪያ የንፅህና ፕላን ማቅረብ ይኖርበታል። ይህም ለምሳሌ እንዴት እርቀትን ማስተናገድ እንደሚቻል፣ በአንድ ጊዜ የተጠቃሚው ብዛት፣ የሳኒታይዘር፣ የማስክ፣ ወዘተ የሚነካኩ እቃዎችን አጠቃቀም፣ ለሰራተኞች ግንዛቤ መስጠትን፣ በርን እና መስኮትን መክፈትን፣ ገንዘብ የሚከፈልበት ቦታ ካለ ይህንን እንዴት እንደሚከለል፣ በየጊዜው ነፋሻ አየር የማስገባትን፣ የስልክ የቪዲዮ ኮንፍረንስ ተደራሽነትን፣ ወዘትን የሚያካትት ይሆናል።

## 10. የገደቦች መላላት - ምሳሌ ምግብ ቤቶች እና የቤት ውስጥ ጂም

ተጠቃሚው ወደ ሪስቶራንቱ ሲገባ ስሙን፣ አድራሻውን እና ስልክ ቁጥሩ ይመዘገባል። እስኪቀምጥ ድረስ ማስክ እንዲያደርግ ይመከራል። ጠረጴዛዎች ተራርቀው ነው የሚቀምጡት።

ዝግ ወይም የቤት ውስጥ ጂሞች ከሆነ ተጠቃሚው አስቀድሞ በኦንላይን ቦታውን ይመዘገባል፣ ሲደርስ የተመዘገበውን ስሙን ያሳያል፣ በተቻለ መጠን በቋሙት ልክ የሆነ ፎጣ የስፖርት መሳሪያዎቹ ላይ ያደርጋል፣ መሳሪያዎቹን ከመጠቀሙ በፊት በሳኒታይዘር ያፀዳል፣ ወደ ሌላ መሳሪያ ሲቀይርም ያፀዳል። በጂም ውስጥ ቁጥራቸው ጥቂት የሆኑ ሰዎች ብቻ ነው የሚገቡት። በመሃከላቸው የ3 ሜትር ርቀት ይኖራል። ለምሳሌ ለአንድ ሰአት ያክል 8 ሰው ይስተናገዳል፣ ጎን ለጎን ሳይሆን በተጠቃሚዎቹ መሃል አንድ የስፖርት መስርያ ማሽን ሰው አይጠቀምበትም። መስኮቶች እና በሮች ነፋሻ አየር ለማስገባት ክፍት ናችው። ሻዎሮች ዝግ ናቸው።

## 11. ቴያትር እና ፊልም

የፊልም ቀርፃዎች በአነስተኛ መልኩ ተጀምረዋል። በፊልም ላይ የሚሳተፉ ሰዎች የኮሮና ምርመራን አስቀድመው ልክ እንደ እግር ኳስ ተጫዋቾች ማድረግ አለባቸው። ቴያትር ቤቶች አልጀመሩም። አንዳንድ ቦታ ላይ በክፍት ሜዳ ላይ የሚታዩ አሉ። የጀርመን ፕሬዝዳንት ሽታየንማየር በቅርቡ ባዶ ቴያትር ቤቶችን በመጎብኘት ማበርታታት አድርገዋል።

## 12. መዘናጋት እና ሰላማዊ ሰልፎች

ሱንሱ (Sun Tzu) የተባለው የሚሊተሪ ስትራቲጅስት እና ፈላስፋ የጦርነት ስልት (The Art of War) በሚል ከሺ አመታት በፊት በፃፈው መፅሃፉ ላይ „ትልቁ አደጋ የሚከሰተው አሸንፌያለሁ ተብሎ በድል ምናብ መዘናጋት ሲፈጠር ነው“ እንዳለው ችግሩን ተወጣነው ወይም አስጊነቱ ቀንሷል በሚባልበት እና መርጋጋት በሚታይበት ጊዜ የተወሰኑ መዘናጋቶች ይታያሉ። በቀላሉ የመሸነፍ አደጋም ይጨምራል። ጀርመን የገደብ መላላት ከተደረገ በኋላ በአሁኑ ሰዓት በአማካይ 360 ሰዎች በወረርሽኙ በቀን ይያዛሉ። ጀርመን የወረርሽኙን የመጀመሪያው ማዕበል መስፋፋትን በማዝገም ከተቋቋሙት በኋላ ገደቦችን በብዛት የማላላቱ እርምጃ ተወስዷል። በዚህም ቁጥሩ እንደገና መጨመሩ ተመዝግቧል።

በሚኒያፖሊስ በግፍ የተገደለውን ጆርጅ ፍሎይድን ለመዘከር እና በጀርመንም የሚታየውን የዕልት ተዕልትና መዋቅራዊ በቆዳ ቀለም ላይ የሚታየውን ዘረኝነት ለመቃወም በጀርመን ከተማዎች በተለይም በበርሊን ተፈቅደው ባየናቸው ሰላማዊ ሰልፎች ላይ የአፍንጫ እና የአፍ መከላከያን ማድረግ ብቻ ሳይሆን ቁጥሩን ለመቆጣጠር እንደሚከብድ እና ርቀትን ለመጠብቅ እንደሚያስቸግር ነው። ይህንንም በተመለከተ የጀርመን ፖሊስ አዲስ ስልቶችን ለማውጣት እያሰበ ነው። ለምሳሌ በሚቀጥሉት ቀናት በሚደርግው ሰልፍ ላይ በተናጠል የሚቆምበት 9 ኬሎሜትር የሚፈጅ ያለንኪኪ የሰንሰለት ሰልፍ ለመፍቀድ እያታሰብ ነው።



Dr. Tsegaye Degineh, H: www.degineh.de, E:mail@degineh.de፣ T: @TsegayeD4, F: fam.degineh

## 13. አሸብላይ መልዕክቶች እና የሴራ አይዲውሎጂ

የኮቪድ 19 ወረርሽኝን በተመለከት በማህበራዊ ሜዲያ ላይ በከፍተኛ ፍጥነት የተስፋፋው እና እርስ በርሱ የሚቃረነው ከንስፐረሲ/የማሴር ቴዩሪ ወይም አይዲዮሎጂ ነው። ይህም የመሸብለል ሳይኮሎጂን (Manipulation Psychology) በመጠቀም በቀላሉ ፍራቻን በመፍጠር እና ወደፊት በሚከሰተው ላይ ጥርጣሬ እንዲፈጠር በማድረግም፣ ከኋላው ድብቅ አጀንዳ እና አንድ ልዩ ሃይል አለ በማለት ሰውን ማሸብለል ነው። ይህም ወደ ቡድን ሲያድግ ደመነፍሳዊ የማሰገድድ አንደምታን ይጨምራል። በ14ኛው ክፍለ ዘመን የአውሮፓን አንድ ሶስተኛ ህዝብ የጨረሰው ጥቁር ሞት መንስኤ አይሁዳዎች ናቸው የሚለው የሴራ ቲዮሪ በመስፋፋት ለብዙ አይሁዳዎች መሰደድ እና እልቂት ሆኖ ነበር። ይህም አንድን ሐሰት አብዛኛው ሰው ስለተከተለው ብቻ እውነት ነው ብሎ መቀበልን መሪ የሚያደርግ ሁኔታን ነው (Conformity Theory)። የማሳመኛ ቴክኒኮችን ከወሰድን ደግሞ „ከአጠቃላዩ ወደ ውስኑ“ የሚሂዱ መሰረታዊ ማሳመኛዎች (Argumentum a priori) ሳይሆኑ ትንሽ እውነትን ይዞ ለተሳሳተ ማስረጃና ማጠቃልያ በመጠቀም (false conclusion, sophismus) ወይም እገሌ እንዳለው በማለት (Argumentum ad verecundiam) ማሸብለልን ነው። ሌላው ደግሞ ፍታሃዊ ያልሆነ ማነፃፀር ነው። ለምሳሌ የኮሮናን ሞት ከመኪና አደጋ ሞት ጋር አይየዞ ማነፃፀርያ የሚያቀርብ በቅድሚያ የከፋ የመኪና አደጋ እንዳይፈጠር ሰውና መኪና አብሮ እንደማይሄድ፣ መንጃ ፈቃድ እንደሚያስፈልግ፣ የመኪና ምልክቶች እና ደንቦች፣ የመኪና የደህንንነት ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸው እና ይህ ሁሉ ታልፎ አደጋ እንደሚፈጠር አይገልፅም። ይህ ማለት በኮሮና በኩል ለማነፃፀር እንዲቻል ወረርሽኙን ለመቋቋም ብዙ ነግሮች መሰራት እንዳልባቸው አይገልፅም ወይም አያምንም። በቅርቡ በዋትሳአፕ (WhatsApp)፣ ቫይበር (Viber) በመሳሰሉት ወዘተ የሚሰራጩት የፈጠራ፣ አጓጉዊ እና የአጥማጅነት ባህሪያ ካላቸው መልዕክቶች (*hoax* and phishing *messages)* አንዱ የቻይና ማስክ ኢትዮጵያ ውስጥ ወረርሽኙ እንዲስፋፋ እንዳደረገ ነው። እንግዲህ ይህ ማስክ ነው አውሮፓ ውስጥ በሽታው ያውም መቀንስ ከተጀምረ በኋላ ከቻይና የገባው እና እድገቱም እየቀነሰ ያለው። የፈጠራ / ሆክስ መልዕክቶች የሚታውቁት ይህንን መልዕክት ይህንን ያህል ቁጥር ላላቸው ሰዎች አስተላልፍ ወይም ከአስተላለፍክ መልካም ነገር ታገኛልህ ወዘተ የሚል በፍራቻ እና በጉጉት ተሞርኩዞ በፍጥነት የሚተላለፉ ናቸው። እዚህ ላይ አምኖ ከመቀበል በፊት ማጣራት (fact check)፣ መጠየቅ፣ የሚወንጀልም ካለ የተወንጃዩን ሃሳብ ለሚዛናዊነት መስማት ያስፈልጋል።
በከንስፐረሲ/የማሴር ቴዩሪ በቀላል የእምነት ደርጃ ላይ የሚገኙቱን ሰዎች በማስረጃ መመለስ እንደሚቻል ሲታውቅ በጣም ጠልቀው የገቡትን ግን ለማሳመን እና ለመመልስ መቻሉ እድሉ ኢምንት ነው። ይህ ከላይ የተጠቀሰው ገለፃ በገንቢ ትችት (Constructive Criticism) ለሚያቀርቡ፣ በሃሳብ እና በነጥቦች ላይ ማሻሻያን ወይም የተለየ ሶስተኛ አስተያየት እና ጥያቄን የሚያነሱትን እንደማይመለከት ግልፅ ይመስለኛል።

የጀርመን ደህንነት፣ የአገር ውስጥ ጉዳይ እና „የህገ መንግስት ጠባቂ“ አካል የህዝቡን ደህንነት እና ሰላምን ለመጠበቅ በቀኝ አክራሪዎች፣ በከንስፐረሲ አይዲዮሎጂስቶች እና በውጭ አገር የስለላ ተቋማት በተለያየ መልኩ እየተሰራጨ ያለውን የተሳሳተ ዜና፣ ጫና ለመፍጠር፣ ገደቦችን ለመጣስ ረብሻን ማዘጋጀት እና ማደናገሮችን በጥብቅ እንከታተላለን ሲሉ በዚህ ሳምንት ተገልጿል። ከጀርመን ውጭ ለሆኑ አንባቢዎች ለመግለፅ ያህል የህገ መንግስት ጠባቂ (Verfassungsschutz) የሚባለው ተቋም አንዱ ዓላማው አባሎቹ የወንጀለኞች ቡድንን፣ ተጠርጣሪዎችን ተቀላቅለው እና ቀርበው ወይም ሰርገው፣ የቀኝ እና የግራ ፅንፈኛ ቡድን አባል እና አመራርም በመሆን ለረዥም ጊዜ ድርጊቱን የሚከታተሉ እና የጀርመን ህዝብ እና ህገ መንግስት አደጋ ላይ እንዳይጋረጥ የሚከለከሉ ናቸው። ሌላው የጀርመን ፖሊሶች የዲጂታል አሻራ መከታተያ ቴክኖሎጂን በመጠቀም በእውነተኛም ሆነ በድብቅ ስም በሶሻል ሜዲያ የሚያሰረብሽ እና የጥላቻ ዜናዎችን የሚያስተላልፉትን በጥብቅ መከታተል ጀምረዋል። ከወረርሽኙ ጋር ባያገናኝም ለግንዛቤ እንዲረዳ ለመጥቀስ ያህል ለምሳሌ ባለፈው አመት የተገደሉትን የካስል ከተማ ዲስትሪከት ፕሬዝዳንትን በሟቹ ስም ላይ በፌስቡክ የጥላቻ እና ስድብ መልዕክት ባስተላልፉ 40 ሰዎች ላይ ከቀናት በፊት የጀርመን ፖሊስ በተለያዩ ስቴቶች ባደርገው የተቀናጀ የቤት ለቤት ፍተሻ ተጠርጣሪዎችን፣ ኮምፒውተሮችን እና ስማርትፎኖችን ይዟል።



Dr. Tsegaye Degineh, H: www.degineh.de, E:mail@degineh.de፣ T: @TsegayeD4, F: fam.degineh

## 14. የበጎ ፈቃድ አገልገሎት

ጀርመን ውስጥ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ምግብ ከሚያቀርቡ 949 የምግብ ባንኮች ግማሹ ቢዘጉም ተርጂዎችን ለማዳርስ የተለያዩ በጎፈቃደኞች ያላሰለሰ ስራ ሰርተዋል። ጀርመን በከፍተኛ ችግር ላይ ቢገኝም ከራሳቸው አልፈው አፍሪካን በመርዳት በተለይም ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ለወረርሽኙ መቋቋሚያ እንዲሆን በሚያዚያ ወር የጀርመን መንግስት 120 ሚሊዮን ዮሮ መርዳቱ አይዘንጋም። ይህም እርስ በእርስ መርዳዳት ምን ያህል መሰረታዊ ተግዳር መሆኑን ያሳየናል። ጀርመኖች በበጎፈቃደኛ ማህበራት በከፍተኛ ሁኔት የተደራጁ ናቸው። በጀርመን 27 ሚሊዩን ሰዎች ወደ 580 ሺ የበጎ ፈቃድ ማህበራት ውስጥ ሲኖሩ ለምሳሌ ከ4 ሰዎች አንዱ 90ሺ በሚሆኑት የስፖርት ማህበራት በአንዱ በበጎ ፈቃደኛነት ያገለግላል። ኢትዮጵያ የገዳ ስርዓት፣ የደቦ፣ የዕድር፣ የዕቁብ፣ የአፈርሳታ፣ የአውጫጭኝ፣ የህብረት ስራ ማህበራት ታሪክ ያላት ናት። እንደጀርመንም በጎ ፈቃድ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን እና ተጓዳኝ ችግሩን ለመቋቋም ለኢትዮጵያ የማህበረሰቡ አንድ ምሶሶ መሆን ይችላል። እዚህ ላይ አዲስ አበባ ውስጥ በ2012 ክረምት በተለያዩ ዘርፎች በሰብአዊ አገልግሎት ፕሮግራሞች ላይ የበጎ ፈቃድ መርሀ ግብር በማቀድ ከአንድ ሚሊየን የበጎ ፈቃደኞች ለማሳተፍ መታሰቡ የሚመሰገን ሲሆን ይህን መሰል ዕቅድም በተለያዩ ቦታዎችም መጠቀም ያስፈልጋል።

## 15. ለይቶ ማቆያ፣ የኮሮና ቫይረስ ሪፖርት፣ የጤና ባለሙያዎች

የባህሪይ እና የአስተሳሰብ ለውጥ ላይ ብዙ መሰራት ይገባል። ለይቶ ማቆያ/ማገገሚያዎች የማያስፈልጉብትን ዘዴ በመፈጠር ሰው ከተያዘ በኋላ በራሱ ሃላፊነት እቤቱ የሚቆይበትን ሁኔት እንደሚታሰብበት እርግጠኛ ነኝ። ቁጥሩ እየበዛ ሲሄድ ይህ የማይቻልበት ደርጃ ይደርሳልና። እንኳንስ ተይዞ ሳይያዝም ራስን የማግለል የግል ሃልፊነት ተደርጎ መወሰድ አለበት። የግል ምሳሌ ለመጥቀስ እድሜያቸው ሰባዎቹ ውስጥ የሚገኙትን በህክምና ዘርፍ የምትሰራው የጀርመናዊ ባለቤቴን ወላጆች ለረዥም ጊዜ ስላላየን እንሱን ለመጎብኘት እና ለመርዳትም ከበርሊን 400 ኬ.ሜ. ርቀው ወደሚኖሩበት መንደር በዚህ የአውሮፓ በጋ ላይ ከመሄዳቸን በፊት በፈቃደኝነት ራሳችንን ለ14 ቀናት እቤት በማቆየት ለማግለልና ከመጓዛችን በፊት ለመመርመር ወስነናል።

ባለፈው እንደገለፅኩት ኢትዮጵያ ለሜዲያ በሚቀርበው ሪፖርት ላይ የተያዙትን ሰዎች ዜግነት መግለፅ በመጀመሪያ ተገቢ ቢሆንም ቁጥሩ እየበዛ ሲመጣ ግን ከእድሜ፣ ከፆታ እና ከተገኘበት አካባቢ በተጨማሪ ዜግነትን መጠቀሱ ቢቀር የሚል አስተያየት አለኝ። ይህ ጀርመን አገር ጥንቃቄ የሚያሻው (senstive) ርዕስ የሆነ እና የማይታሰብ ነው። በተጨማሪም አንድ የጤና ባለሙያ ወረርሽኙ ቢይዘው የሚሰራበት ክፍል በሙሉ መዘጋት አለብት ወይ የሚለው ላይ ቢጠናበት መልካም ነው። ሌላው ደግሞ አንድ ሰው ፖዘቲቭ ከሆነ የሚኖርበት አካባቢ በምንም አይነት መልኩ ለተጠቂው መጥፎ እይታ ሊሰጥው የማይገባበትን ግንዛቤን ማስያዝ ያስፈልጋል።

## መደምደሚያ

ይህ ፅሁፍ ኢትዮጵያን ከጀርመን ጋር ለማንፃፀር ሳይሆን በወረርሽኙ የተነሳ በጀርመን ላይ የደርሰውን ከፍተኛ ቀውስ ለመወጣት የሚደረገውን ሂደት ልምድ ለመውሰድ፣ ስለ በጎፈቃደኝነት፣ ስለመሰርታዊ ፍጆታ ቀጣይነት፣ ህዝብን ስለማስተባበር፣ ስለመዘናግት እና የማሸብለል ስጋቶችን፣ ስለሚወስዱ የስራ ቅደም ተከተል እና የአፈፃፀም ምሳሌዎችን ግንዛቤ ለመጨበጥ እንዲያስችልም ነው። በዚህ ፅሁፍ ላይ የሚያሻሽልና ተጨማሪ ሀሳብ የሚያቀርብ መልካም ነው።

ደከመኝ ሰልቸኝ ሳይሉ በመልፋት የሚቻላቸውን ሁሉ ለሚያደርጉት **የኢትዮጵያ የህክምና ባለሙያዎች** እና **የኢትዮጵያ ጤና ኢንስቲትዩት** የተለመደውን ትልቅ ምስጋናዬን አቀርባልሁ።

ዶ/ር ፀጋዬ ደግነህ ጉግሳ
በርሊን ሰኔ ፯ ፪ሺ፩፪ ዓ.ም. (*Berlin, 14 th June, 2020*)



Dr. Tsegaye Degineh, H: www.degineh.de, E:mail@degineh.de፣ T: @TsegayeD4, F: fam.degineh